**በመንግሥት ት/ቤቶች የመምህራንን ቅጥር በሚመለከት የወጣ መመሪያ ቁጥር 86/2013**

ሀገራችን አሁን ከምትገኝበት ዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታ ተላቃ ሕዝቦችዋ የተሻለ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሕይወት እንዲመረ መንግሥት ልዩ ልዩ ርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል። በተለይ ድህነትንና ኋላቀርነት ባጭር ጊዜ በማስወገድ በምትኩ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው አስተማማኝ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማረጋገጥ የድህነት ቅነሳና የዘላቂ ልማት ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው።

ለድህነት ቅነሳና ለዘላቂ ልማት መረጋገጥ ትምህርትና ሥልጠና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። በተለያዩ ሙያዎች በመለስተኛ፣በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ሃይል ለማፍራት፣ ዘመናዊ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶች በአግባቡ ተጠቅሞ የተሻለ የሚያመርትና ኑሮውን በአስተማማኝ የሚለውጥ እብረተሰብ ለመገንባት ትምህርት ከፍተኛውን ሚና ይጫወታል።

ለዚህም በየደረጃው የሚሰጠው ትምህርትና ሥልጠና ጥራቱ የተጠበቀ መሆን አለበት። ሶስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር ለትምህርት ጥራት ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ የመምህራንን ጥራት ማረጋገጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው። በመሆኑም ለመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል።

የመምህርነት ሙያ ዜጐችን በአስተማማኝ ዕውቀት፣ ክህሎትና በመልካም አስተሳሰብ አንጾ የማውጣት ከባድ ኃላፊነት ነው። ለዚህ ከባድ ኃላፊነት የሚያበቃውን መምህራንን ትምህርትና ሥልጠናን ከምልመላ ጀምሮ በጥንቃቄ ማከናወን፣ ጥራት ያለው ሥርዓተ ትምህርት በመቅረጽም በቅድመ ሥራ ሥልጠና በሙያው በቂ ዕውቀትና ክህሎት እንዲጨብጡ ማድረግ እንዲሁም ፕራክቲከምን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

የመምህራን አሠለጣጠን መዘበራረቅ በመምህራን ብቃት ላይ ብሎም በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ በሁሉም የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ተመሣሣይነት ያለው ወጥ ሥልጠና እንዲሰጥ ማድረግ በሙያው የተካኑ መምህራን ማፍራት ያስፈልጋል።

ከግል ተቋማት የተመረቁ መምህራን የነበረብንን የመምህራን እጥረት ችግር በመቅረፍ አስተዋጽኦ ያደረጉ ቢሆንም በተለያዩ የግል ተቋማት መምህራንን በዕኩል ደረጃና ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ በጥራት አሠልጥኖ በማዘጋጀት በኩል ችግሮች መታየታቸው ይህ ችግር ከእንግዲህ እንዳይከሰት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

የተለያዩ ሀገሮች ልምድ የሚያሳየው የመምህራንን ሥልጠና ሙሉ በሙሉ መንግሥት ብቻ እንደሚካሄድ በመሆኑ በኛም ሀገር በተመጣጣይ የመምህራን ሥልጠናን በመንግሥት ተቋማት በጥራት በማካሄድ በመንግሥት ት/ቤቶች መምህርነት በመቅጠር ለችግሮቻችን መፍትሔ ማስገኘት አስፈላጊ ሆኗል።

በመሆኑም የመንግሥት ት/ቤቶች ጥራት ያለው ትምህርት በመስጠት ብቃት የተላበሱ ዜጎችን ማፍሪያ ማዕከላት እንዲሆኑ የሚቀጠሩ መምህራን ተፈላጊውን ዜጋ ጥራት ብቃት የተላበሱ እንዲሆኑ ለማስቻል ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ዓላማ

የሀገራችንን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ የተቀረፀውን የድህነት ቅነሳና የዘላቂ ልማት ስትራቴጂን በአስተማማኝ ተግባራዊ ለማድረግ በንቃት የሚሳተፍና አስተማማኝ ውጤት ለማስመዝገብ ብቃት ያለው ዜጋ ለማፍራት፣

በሁለተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃግብር የተጣለውን የትምህርት ጥራትን የማስጠበቅ ግብ አስተማማኝ ለማሳካት፣

በመምህርነት የቅድመ ሥራ ሥልጠና አስተማማኝ ዕውቀትና የሙያ ክህሎት የተላበሱ ፕራክትከምን በአግባቡ የተከታተሉና ይህንንም ከት/ቤት ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ተማሪዎችን የማብቃት ክህሎት የተላበሱ መምህራንን ወደ ሙያው ለማስገባት፣

ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትን በዕውቀት፣ በክህሎትና በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፀ፣ የችግር ፈቺነትን አቅም የገነባና በራሱ የሚተማመን ብቁ ዜጋ ማፍራት ሙያዊ ተክህኖ የተላበሱ መምህራንን በጥራት አፍርቶ ወደ ሥራው ዓለም ለማሠራት፣

እስካሁን ያለው የተዘበራረቀ የመምህራን አሠለጣጠን በትምህርት ጥራት ላይ ያሳደረውን አሉታዊ ተጽእኖ በማስወገድ በተመሣሣይና ወጥ አሠለጣጠን የተመረቁትን መምህራን ወደ ሥራው ዓለም ለማሠማራት፣

## ክፍል ሁለት

## ጠቅላላ

### አጭር ርዕስ

መመሪያ በመንግስት ት/ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ከመንግስት መምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የተመረቁ ዕጩ መምህራን ብቻ እንዲሆኑ ማድረግ የወጣ የትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 86/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አውጪው ባለሥልጣን

የትምህርት ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ሃላፊነት ለመወሰን በወጣው ቁጥር ________መሠረት ይህን በመንግስት ት/ቤቶች የሚቀጠሩ መምህራን መንግስት የመምህራን ትምህርትና ተቋማት የተመረቁ ዕጩ መምህራን እንዲሆኑ የሚያደርግ መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. ‘’ትምህርት ሚኒስቴር’’ ማለት የፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ነው፡፡
2. ‘’ሚኒስትር’’ ማለት የፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ነው፡፡
3. ‘’ቴክኒክና‘’ትምህርትና ስልጠና ኮሚሽን’’ማለት በፌዴራልና በክልል አስተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አመራር አስተዳደርን የሚመራ አካል ነው፡፡
4. ‘’የግል ተቋማት’’ማለት የመምህራን ትምህርትና ሥልጠናና የሚያካሂዱ የግል ተቋማት ናቸው፡፡
5. ‘’ስልጠና’’ ማለት የመምህርነት ሙያ የሚያበቃ ስልጠና ነው፡፡

6. "የመንግሥት ተቋማት" ማለት የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና የሚያከናውኑ በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ ተቋማት ናቸው።
7. "ሠልጣኝ" ማለት በመምህርነት ሙያ ለመሰማራት በሥልጠና ላይ ያለ ተማሪ ነው።
8. "ፖሊሲ" ማለት አገር አቀፍ የትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ ነው።
9. "ኤጀንሲ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት ጥራት ኤጀንሲ ነው።
10. "የሥራ ፈቃድ" ማለት በከፍተኛ ትምህርት አግባብነት ጥራት ኤጀንሲ ወይም በቴክኒክና ሙያ ኮሚሽን ወይም እንደሁኔታው በክልል ትምህርት ቢሮ የሚሰጥ እውቅናና ቅድመ እውቅና ነው።
11. "የሙያ ፍቃድ" ማለት መምህራን ሙያ የሚጠይቀውን መመዘኛዎችን መሟላታቸው በማረጋገጥ የሚሰጥ ፈቃድ ነው።
12. "ፕራክቲከም" ማለት በስልጠና ላይ ያሉ እጩ መምህራን ሙያዊ ልምምዶች የሚያከናወንበት መርሀ ግብር።

## ክፍል ሦስት

## አጠቃላይ ድንጋጌ

1. የመምህርነት ሙያ ሥልጠና ፖሊሲ አቅጣጫና ዓላማ በፌዴራል የትምህርት ሚኒስቴር ይቀረፃል።
2. ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በመንግሥት ት/ቤቶች በመምህርነት የሚቀጠሩት በመንግሥት ተቋማት በሙያው የሠለጠኑ ብቃታቸው የተረጋገጠላቸው ዕጩ መምህራን ብቻ ይሆናሉ።
3. መምህራን በሙያው ለመቅጠር ለማገልገል የማስተማር ሥራ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው፣ ይህም በመንግሥት ተቋማት በኩል የሚፈፀም ይሆናል።

## ክፍል አራት

## የሽግግር ስልቶች

የዕውቀና /የቅድመ ዕውቀና/ ፈቃድ ተሰጥቷቸው መምህራንን በሚያሠለጥኑ የግል ተቋማት የሠለጠኑትንና በማሠልጠን ላይ የሚገኙትን ዕጩ መምህራንን በተመለከተ የሚከተለው ተግባራዊ ይደረጋል።

4.1 ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋል በፊት በግል ተቋማት በመምህርነት ሙያ የሠለጠኑትን በመሠልጠን ላይ ያሉ ዕጩ መምህራን ለመምህርነት ሙያ የተቀመጠው ስታንዳርድ ከሟሉ ብቻ በመንግሥት ት/ቤቶች ሊቀጠሩ ይችላሉ። /ዝርዝር ስታንዳርድ የአፈፃፀም ሁኔታ ወደፊት የሚገለጽ ይሆናል።/

4.2 ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በመምህርነት ሙያ በግል ተቋማት ሠልጥነው የሚወጡ ተማሪዎች በመንግሥት ት/ቤት በመምህርነት አይቀጠሩም። ሆኖም በግል ት/ቤቶች በመምህርነት ሊቀጠር ይችላሉ።

## ክፍል አምስት

## መረጃን በተመለከተ

5.1 በግል ተቋማት በ10+1እና 10+2 መርሀግብሮች እንዲሁም በዲግሪ መርሃግብር በመምህርነት ሙያ ሥልጠና ጀምረው በልዩ ልዩ ምክንያቶች ያቋረጠ ተማሪዎችን ዝርዝር መረጃ አሰልጣኝ ተቋሙ የዕውቅና /የቅድመ ዕውቅና ፈቃድ በአለው አካል እስከ ሰኔ 10 ቀን1999 ዓ/ም ድረስ ማሳወቅ አለበት።

5.2 በ10+3 እና በዲፕሎማ መርሃ ግብር በመሠልጠን ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ዝርዝር መረጃ አሠልጣኝ ተቋሙ ፍቃድ ለሰጠው አካል እስከ ሰኔ 10 ቀን 1999 ዓ/ም ማሳወቅ አለበት።

5.3 ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 5.1 እና 5.2 በተመለከተ መሠረት አሠልጣኝ ተቋሙ የአቋረጡትንና በመማር ላይ የሚገኙት ተማሪዎች ዝርዝር በተጠቀሰው ጊዜ ማቅረብ የሚገባው 10+3 መርሃ ግብር ተማሪዎችን መረጃ በክልሉ ለተጠሰው አካል ሲሆን የዲግሪ መርሃ ግብር ተማሪዎች ዝርዝር ደግሞ ለከፍተኛ ትምህርት ጥራት አግባብነት ኤጀንሲ ይሆናል።

5.4 በክልሉ ፈቃድ ለሰጠው አካል ሲሆን ፣የዲግሪ መርሃ ግብር ተማሪዎችን ዝርዝር ፣ረጃ ደግሞ ለከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## የግል ተቋማትን በተመለከተ

6.1 በዚህ መመሪያ መሠረት በመንግስት ት/ቤቶች ስለሚካሄድ የመምህራን ቅጥር አቅጣጫ የግል ተቋማት ሃላፊዎች (የግል ባለሀብት) እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡

6.2 መምህራንን ለማሠልጠን ህንጻ የገነቡ፣ መምህራን የቀጠሩ ፣ ቤተ ሙከራ፣ ቤተ መጻሕፍት ወዘተ …. ያደራጁ የግል ተቋማት በሌላ የሥልጠና መስክ እንዲሠማሩ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

7. ይህን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የክልል መንግስታት የክልላቸውን ሁኔታ ያገናዘበ የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣሉ፡፡

8. የተፈጻሚነጽሻን

8.1 ይህ መመሪያ በቀን መደበኛ መርሃ ግብር ፣በማታው መርሃ ግብርና በርቀት መርሃ ግብር በሚሠለጥኑ መምህራን ላይ፣

8.2 በርዕሠ መምህርነት፣ በሱፐርቫይዘርነት፣ በትምህርት አመራርና አስተዳደር እንዲሁም ከትምህርት ሥራ ጋር አግባብነት ባላቸው ሙያዎች በሠለጠኑና በሚሠለጥኑ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

9. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ____________ጀምሮ የጸና ይሆናል ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር

___________ቀን 1999 ዓ.ም

አዲስ አበባ